# የShoreline የስኩተር እና የብስክሌት መጋራት የሙከራ ፕሮግራም

የShoreline ከተማ በከተማው የትራንስፖርት ይዘት እና የአየር ንብረትን የሚመለከት ስራ መርሃ ግብር ውስጥ ለዘላቂ መጓጓዣ ያለንን ቁርጠኝነት በመደገፍ የስኩተር እና የብስክሌት መጋራት የሁለት አመት የሙከራ መርሃ ግብር በማስጀመራችን በጣም ደስ ብሎታል።

ፕሮግራሙ እስከ ኦገስት 2026 ድረስ ይቆያል፣ 50 ብስክሌቶችን ጨምሮ በ Lime በሚንቀሳቀሱ 200 መሳሪያዎችም ላይ ይጀምራል (ከፍተኛው የመሳሪያዎች ብዛት 400 ነው)።

**ቅድሚያ ለደህንነት!**

- አሽከርካሪዎች 18 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ መሆን አለባቸው።
- Lime በአስተማማኝ የስኩቲንግ ተሞክሮዎች ላይ የውስጠ-መተግበሪያ መመሪያን ይሰጣል።
- ሄልሜቶች በLime አስፈላጊ ናቸው እንዲሁም በከተማውም በጣም ይበረታታሉ።
- በጉዞዎ ላይ ሄልሜት ማድረግ የ10% ቅናሽ እንዲኖር ያደርጋል - በLime መተግበሪያ የሚረጋገጥ።

**ስኩተርን ያግኙ እና ይከራዩ**

- የLime መተግበሪያን ለiPhone ወይም ለAndroid ከ (https://www.li.me/) ላይ ያውርዱ።
- ስኩተርን በመተግበሪያው በኩል ያግኙ ወይም በከተማው ዙሪያ ፓርክ የተደረገ ያግኙ።
- በእጅ መያዣው ላይ ያለውን ባለ 6-አሃዝ የQR ኮድ በስልክዎ ካሜራ ይቃኙ ወይም በራስዎ ያስገቡት።
- ጉዞዎን ይጀምሩ።

**ዋጋ + ክፍያ፡**

- Lime መተግበሪያ ለመክፈት 1 ዶላር እና በደቂቃ 0.45 ዶላር ያስከፍላል (በሙከራው ወቅት ሊቀየር ይችላል)
- Lime ወርሃዊ የደንበኝነት ምዝገባዎችን እና ጥቅሎችን በቅናሽ ዋጋ ያቀርባል - Lime (https://www.li.me/)ን በመጎብኘት ለተጨማሪ መረጃ መተግበሪያውን ያውርዱ።
- የቅናሽ ዋጋ (ሊቀየር የሚችል)፡ ለመክፈት $0.75 እና $0.01 በደቂቃ ለLime Access ተጠቃሚዎች፤ የደጋፊ ምግቦች እርዳታ ፕሮግራም (Supplemental Nutrition Assistance Program, SNAP)፣ ሴቶች፣ ጨቅላዎች እና ህጻናት (Women, Infants, and Children, WIC)፣ Medicaid፣ ድጎማ መኖሪያ ቤት ተጠቃሚዎች። ዘመናዊ ስልክ ሳይስፈልግዎት መመዝገብም ይችላሉ። እዚህ ይመዝገቡ፡ https://www.li.me/why/community/lime-access።

**የፍጥነት ገደቦች**

- ስኩተሮች፡ 15 ማይል በሰዓት
- ብስክሌቶች፡ 20 ማይል በሰዓት

**የት ማሽከርከር እንደሚችሉ፡**

- የአገልግሎት አካባቢ ካርታ በLime መተግበሪያ (https://www.li.me/) ውስጥ ይገኛል- ይህም ወደ Seattle የሚሄዱ እና የሚነሱ ጉዞዎችን ያካትታል።
- በShoreline 35 ማይል በሰዓት ወይም ከዚያ በላይ በሆነ መንገድ መንዳት አይቻልም።
- በፓርኮች ውስጥ መንዳት አይቻልም።
- እንደ የህዝብ መገልገያዎች፣ መናፈሻዎች፣ መሻገሪያዎች፣ የትምህርት ቤት ዱሮዎች ባሉ በተመረጡ ዞኖች ውስጥ መንዳት አይቻልም።

**የት ማቆም እንደሚችሉ፡**

- የብስክሌት መደርደሪያዎች።
- ከእግረኛ መንገድ (ከእግረኛ መንገድ ወጥቶ ቀጥ ያለ) አጠገብ ያለው የከርብ/የመልክዓ ምድር ንጣፍ።
- ተመራጭ ስኩተር/የባይክሼር የፓርክ ዞኖች (በ Lime መተግበሪያ ውስጥ በ"P" ምልክት የተደረገባቸው)።

**አያቁሙ ወይም ብሎክ አያድርጉ፡**

- የእግረኛ መንገድ ወይም የእግረኛ መዳረሻ እና የህዝብ መቀመጫ በታዎች።
- የአካል ጉደትኛ አሜሪካዊያን ህግ (Americans with Disabilities Act, ADA) መዳረሻ መወጣጫዎች እና ሌሎች መገልገያዎች።
- የትራፊክ መስመሮች፣ የእሳት አደጋ መስመሮች፣ የአውቶቡስ መስመሮች፣ የብስክሌት መስመሮች ወይም መንገዶች።
- ከእሳት ማጥሪያ ማጓጓዣዎች እና ከህንጻ የእሳት መዳረሻዎች እና ከአውቶቡስ መጠለያዎችን ወይም ከመቆያ ቦታዎችን ይራቁ።
- ያለፈቃድ በግል ንብረት ላይ።

**ችግሮችን ለLime በሚከተለው አድራሻ ሪፖርት ያድርጉ፡ Support@li.me ወይም 1-888-546-3345**

***በሰላም ያሽከርክሩ እና በጉዞዎ ይደሰቱ!***

## የShoreline ቅናሽ ኤሌክትሪክ

# የስኩተር እና የብስክሌት መጋራት

ለቅናሽ ጉዞዎች ለመመዝገብ ብቁ መሆንዎን እና በብቃት ማሟያ ፕሮግራም ውስጥ መመዝገብዎን ያረጋግጡ።





**በዘመናዊ ስልክዎ ላይ ባለው መተግበሪያ ስኩተሮችን እና ብስክሌቶችን ያግኙ**

**ቅናሽ ይመዝገቡ አገናኝ**

Lime

**ብስክሌት እና ስኩተር**

$0.75 ለመክፈት፣ $0.01 በደቂቃ ለማሽከርከር

*(እላይ ለተቀመጠው የዋጋ ቅናሽ ብቁ ለሆኑ ተጠቃሚዎች ነው)*



እርዳታ ከፈለጉ ወይም ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣
እባክዎን ለLime ይደውሉ ወይም ኢሜይል ያድርጉ

ስልክ: 1-888-546-3345 ኢሜይል: Support@li.me